# ወቅታዊ የሃገራችንን ሁኔታ ትንታኔ መሰረት ያደረገ የፀጥታ ዕቅድ

Addis Standard

ጥቅምት 2010 ዓ/ም

አዲስ አበባ

I. መግቢያ

II. የዕቅዱ መነሻ ሁኔታ

1. ውስጣዊ ሁኔታ

1.1 የፌደራል ሥርዓታችንን የሚፈታተኑ ክስተቶች እየተስተዋሉ ነው

1.2 በየጊዜው በሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ ሰብአዊና ማቴሪያላዊ ጉዳት መድረሱን

1.3 ግጭቶች ሃገራዊና ክባቢያዊ መልክ እየያዙ ነው

1.4 የሃገሪቱ ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ እተጎዳ ነው

1.5 የህግ የበላይነት እየተከበረ አይደለም

1.6 የሃገሪቱ ገፅታ እየተበላሸ ነው

Addis Standard

1.7 ግጭቶቹ የመቆም አዝማሚያ አይታይባቸውም

1.8 ህዝቡ ሥጋት ውስጥ ወድቋል

1.9 የችግሩ ባለቤት አሁንም አመራሩ ነው

1.10 የፀጥታ ኃይላችንን ዝግጁነት በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳው ነው

III. የሁኔታ ድምዳሜ

IV. ከድምዳሜ የሚነሳ ዕቅድ

V. ዓላማ

VI. ግቦች

VII. ግቦቹን ለማሳካት የሚሰሩ ስራዎች

VIII. ስራዎች የተሳኩ እንዲሆኑ መከተል ያለብን የመፍትሄ አቅጣጫዎች

1. ህዝቡን ዋነኛ የመፍትሔ አካል አድርጎ መውሰድ

2. ሁሉም ስራዎቻችን ህግንና ስርዓቱን ተከትሎ እንዲፈፀሙ ማድረግ

መንግስት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ መደገፍ

4. ሚዲያ

**X. ስራዎቻችንን ለመስራትና በአግባቡ ለማከናወን ያሉን ምቹ ሁኔታዎች**

8.1 የህዝቡ የሠላም ፍላጎት አሁንም በከፍተኛ ደረጃ መኖሩ

8.2 የውጭ ፀረ-ሠላም ኃይሎች ተፅእኖና ትኩረት አናሳ መሆን

8.3 የፀጥታ አካላት የመፈፀም አቅማችንና ውስጣዊዊ ሁኔታችንአስተማማኝ መሆኑ

8.4 መንግስት ችግሮችን የመፍታት አቅምና ተሞክሮ ያለው መሆኑ

**<. የአፈፃፀም አቅጣጫ**

**<I. ዝርዝር አፈፃፀም**

Addis Standard

## I. መግቢያ

ሀገራችን የነደፈችውን ሁለተኛው የ5 ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን የተመቻቸ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በማድረግ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ግንባታ የእምርታ ጉዞው እንዳይቀለበስ ብሎም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የሃገራችንን የሰላምና መረጋጋት አደጋዎች (የፀጥታ ስጋቶች) እና ተጋላጭነታችንን በአግባቡ በመተንተንና የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት በመንግስት የተነደፈው ሃገራዊ ዕቅድ እንዲሳካ እየታዩ ያሉትን ከፍተኛ የማስፈፀም ድክመቶችና የፀጥታ ችግሮች ማስተካከል የግድ ይላል፡፡

Addis Standard

አሸባሪዎችና ፀረ-ሰላም ሃይሎች ከመቸውም ጊዜና ወቅት በላይ መንግስት የመምራትና የማስፈፀም አቅሙ ተዳክሟል በሚል ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ በተቀናጀና በተወሳሰበ አካሄድና ስልት እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

ዋነኛ አቅማቸውም ህዝባዊ መሰረትና የህዝቦችን የፍትህና የእኩልነት ጥያቄ ሳይሆን መንግስታዊና ድርጅታዊ ድክመቶችንና ተጋላጭነትን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የሠላምና መረጋጋት ችግር መሰረታዊ ምንጭ ውስጣዊ ድክመቶቻችንና ተጋላጭነታችን በመሆናቸው ወሳኙ ሥራ መንግስታዊና ሃገራዊ ቁመናን በሚገባ በማስተካከልና በማጠናከር የህዝብ ጥያቄ የሆኑትን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ መፍታት መጀመር ያስፈልጋል፡፡

ይህንን በሀገር ደረጃ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ጉዳቱ ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይደርስ በአፋጣኝ መፍታት ይጠይቃል፡፡

በዚህ መሰረት የተፈጠረውን ሁኔታ ለማስተካከልና ወደነበረበት የሰላም ሁኔታ ለመመለስ ሁሉንም የፌዴራልና የክልል የፀጥታ አካላት በቅንጅትና ወጥ በሆነ መንገድ ለላቀ ውጤት እንዲረባረቡ ይህ ሀገራዊ የፀጥታ ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

የዕቅዱ ይዘትም የሁኔታ ትንታኔ፣ ግቦች፣ ግቦቹን ለማሳካት የሚሰሩ ዝርዝር ስራዎች፣ የአፈፃፀም አቅጣጫና የቁጥጥር ስርአትን ያካተተ ዕቅድ ነው፡፡

## II. *የዕቅድ መነሻ ሁኔታ*

### 1. ውስጣዊ ሁኔታ

ሁሉም ፀረ ህዝብ ኃይሎች በግብፅና ኤርትራ መንግስታት አዝማችነትና የቅርብ ድጋፍ ተጠቅመው ሥልታዊ የጋራ ግንባር በመፍጠር ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በሁከት፣ በብጥብጥና በአመፅ ለማፍረስ እየተረባረቡ መሆናቸውን ከሁኔታው መረዳት ይቻላል። ለዚህ ምቹ ሁኔታ የፈጠረላቸው ደግሞ በዋናነት በውስጣችን የተከሠተው ተጋላጭነት ሲሆን የተጋረጠውን አደጋ በመቀልበስ ህገ መንግስታዊ የፌደራል ሥርዓቱንና የተጀመረውን ሠላምና ልማት ለማስቀጠል በውስጥ ሁኔታችን ላይ ትኩረት አድርጎ ችግሮቻችን መፍታት የሚጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አኳያ ከላይ በዝርዝር ያየናቸውን ጉዳዮች አጠቃላይ ውስጣዊና ውጫዊ ድምዳሜ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል።

Addis Standard

### 1.1 *የፌዴራል ሥርዓታችንን የሚፈታተኑ ክስተቶች እየተስተዋሉ ነው*

ፌዴራል ሥርዓታችን የህዝቦቻችን ዋስትናና ህልውና መሠረት ሆኖ ቆይቷል፤ በመሆኑም ፌዴራል ሥርዓታችን የህዝቦችን እኩል ተጠቃሚነት ያረጋገጠ፣ ሁሉንም ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመለሰ፣ ልዩነታችን ውበታችን ነው ብሎ አምኖ በመተማመንና በመፈቃቀድ ላይ ያኖረ ሥርዓት መሆኑ፤

ይሁን እንጂ ፌዴራሊዝም አንድነትን የሚያፈርስ፣ የሚበታትን፣ ፌዴራሊዝም በራሱ ችግር ፈጣሪና የሥርዓቱ አደጋ አድርጎ የማየት የተሳሳተ አመለካከት እያደገ መምጣቱ፤ ህዝቡ ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱ የፈቀደለትን በህይወት የመኖር፣ የመንቀሳቀስና ሰርቶ የመኖር ተስፋው እየቀነሰ፣ የመጨለም፣ ተስፋ የመቁረጥና ለመሆኑ ይህ ሥርዓት ይቀጥላል ወይ የሚል ሥጋትና ብዥታ እየፈጠረበት መምጣቱ፤

## 1.2 በየጊዜው በሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ ሰብአዊና ማቴሪያላዊ ጉዳት መድረሱን

ከዚህ በፊት ሲከሰቱ የነበሩ የአዋሳኝ ግጭቶች ምንም ዓይነት ፖለቲካዊ ይዘት ያልነበራቸው፣ ከባቢያዊ፣ ለአጭር ጊዜ ታይተው ወዲያው በህዝቡ ባህላዊ እርቅ የሚያልቁና ፍፁም የሃገሪቱ ስጋት ሆነው የማያውቁ፣ ህገ-መንግስታችን በሚፈቅደው መሰረት የሚካለሉና ወይም በጋራ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው፡፡

በአንዳንድ የሃገሪቱ አካባቢዎች በተለይም በቅርቡ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች ድንበር አካባቢ የነበረው ግጭት ከላይ ከተጠቀሰው በመሰረቱ የተለየ ነው፤ ማለትም

- ሰፊ ህዝብ ከቀዬው ያፈናቀለ
- የጅምላ ጭፍጨፋ የተካሄደበት (Genocide)
- ኢ-ሰብአዊና አሰቃቂ ግድያዎች የተፈፀሙበት
- የህዝቡ የመኖርና የመንቀሳቀስ መብት ስጋት ውስጥ የወደቀበት
- በህዝቦች ሞራላዊና ስነ-ልቦና ላይ ጠባሳ የፈጠረ፣ በአጠቃላይ በሃገራችን ስም የሌለውና ኃላፊነት በግልፅ የማይወስድ ሽብርተኝነት እየተስፋፋ እንዳለ ማየት ይቻላል፡፡

Addis Standard

## 1.3 ግጭቶች ሃገራዊና ከባቢያዊ መልክ እየያዙ ናቸው

**አንደኛ**

- ባለፉት ሁለት ዓመታት በማያባራ ግጭትና ነውጥ ውስጥ ተዘፍቀን ቆይተናል፡፡ አሁንም ችግሮቹ ከሥር መሠረታቸው አልተፈቱም፡፡ በመሆኑም ግጭቶቹ ቀስ በቀስ ሃገራዊና ከባቢያዊ መልክ እየያዙ እየመጡ ነው፡፡

**ሁለተኛ**

- በሁሉም ክልሎች ለግጭት መነሻ የሆኑ ያልተቋጩ አጀንዳዎች መኖራቸውንና ግን ደግሞ ከቦታ ቦታና ከክልል ክልል ደረጃቸው የሚለያዩ መሆናቸውን ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

**<u>ሶስተኛ ደግሞ</u>**

- ዋናው ችግር መንግስት የጀመረውን የጥልቅ ተሃድሶ በተፈለገው ፍጥነት ያመሄድና ዘገምተኛ የመሆን ሁኔታ ስላ ነው፡፡

## 1.4 <u>የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ እየተጎዳ ነው</u>

ያለፉት በርካታ ዓመታት የመንግስታችንና የህዝባችን ትኩረትና አጀንዳ ድህነትን መዋጋት፣ ህዝቡ በየደረጃው ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ሌት ተቀን ሲረባረብና ሲተጋ ነበር፣ አሁንም እየተጋ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ይህን የሚሸረሽሩ ሁኔታዎችና እንቅስቃሴዎች እየተፈጠሩ ናቸው፡፡

- የልማት ወይም ድህነት የማሸነፍ አጀንዳ ወደ ጎን በመተው ህዝቡንና ወጣቱን ወደ ልማት ከማዝመት ይልቅ ወደ ግጭትና ጦርነት ማዝመት፣
- ከዋናው የመንግስታችን አጀንዳና ትኩረት በመውጣት ኢኮኖሚያችንን በሚጎዳ መንገድ መንቀሳቀስ
- በአንዳንድ ኪራይ ሠብሳቢዎች ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር መስፋፋት፣ መሠረታዊ ሸቀጦችን መደበቅና እጥረት መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ መደበቅና ማሸሽ
- አንዳንድ ባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች ገንዘባቸውን ወደ ውጭ ማሸሽ እንዳለም አዳዲስ ጥቆማዎች እየመጡ ናቸው፡፡

Addis Standard

**<u>በዚህ መሠረት፡-</u>**

- የውጭም ሆነ የውስጥ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መቀዛቀዝና መዳከም፣
- የነበረው የቱሪስት ፍሠት በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ፣
- ይገኙ የነበሩ ዕርዳታዎች በስመ ሰብአዊ መብት ጥሰት መቀነስና በጥርጣሬ አይን ማየት፣
- በርካታ ቤቶችና ንብረቶች በግጭቱ መውደምና ተፈናቃዮችን ለመርዳት ከፍተኛ ወጪ መጠየቁ፣
- አግባብነት የሌለው የዋጋ ጭማሪ፣ ኮንትሮባንድ፣ ህገ-ወጥ ንግድ፣ ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር የሃገርን የኢኮኖሚ ደህንነት ከማወኩ በላይ ለህገ-ወጥ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣

ፀረ-ሠላምና አሸባሪ ኃይሎች የፋይናንስና የሎጅስቲክስ አቅም መፍጠሪያ እየሆነ መምጣቱ፤

- መንግስት ለልማት የሚያውለው ግብር በአሁኑ ጊዜ በአግባቡ እየተሠበሠበ አለመሆኑ፤ ለዚህም በአንድ በኩል ተገቢ ያልሆነ ግምት በመጫን ቅሬታ እስኪስተካከል ጠብቁ የሚል ሳቦታጅ መብዛቱ፤ በሌላ በኩል ከሁከቱ ጋር ተያይዞ መንግስት የለም፤ ግብር አትክፈሉ የሚል ማደናገሪያ በመንገሱ፤
- ከሃገር እንዳይወጡ ክልከላ የተደረገባቸው ምርቶች ወደ ውጭ እየወጡ በመሆኑ የሃገር የፍጆታ ምርቶች በመቀነስ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ እያደረገ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

Addis Standard

## 1.5 የህግ የበላይነት እየተከበረ አይደለም

በዚህ ሁለት ሶስት ዓመት በርካታ የህግ ጥሰቶችና ፀረ-ህዝብ ድርጊቶች ተፈፅመዋል፡፡ በተለይም ደግሞ በኢፌዴሪ ፓርላማ በሽብርተኝነት የተፈረጁ እንደ አርበኞች ግንቦት 7 እና ኦነግ የመሳሰሉ ሽብርተኞች እንደፈለጉ የሚፈነጩበትና በህግ የሚጠየቁበት ሁኔታ የለም፡፡ ህዝባችንን ሥጋት ውስጥ እየከተተ ነው፤ ለመሆኑ ችግሩ ይፈታል ወይ ብሎ ተስፋ የመቁረጥ፣ ዋስትና ያለማግኘትና ስጋቶች የመበራከት ሁኔታ ይታያል፡፡

ሌሎች ፀረ-ሠላም ኃይሎችም በተለያዩ መድረኮች የብሄር-ብሄረሰብ ማንነትና አንድነትን የሚገልፅ ሰንደቅ ዓለማችንን ወደ ጎን በመተው ህዝባችንን የማይወክሉ አርማዎችንና ሰንደቅ ዓላማዎችን ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ ለበርካታ ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆኑና በተግባር የተሳተፉ አመፀኞችና ተባባሪዎችም ተይዘው ተመጣጣኝና ህጋዊ እርምጃ አልተወሰደባቸውም፡፡

በርካታ የመንግስትና የህዝብ ሀብት (ተቋሞች) ያወደሙም ተመሳሳይ እርምጃ አልተወሰደባቸውም፡፡ የብሔርና የጎሳ ግጭቶች ያስከተሉት ደም መፋሰስና የንብረት ውድመት ተከትሎ በየደረጃው ተጣርቶ የሚወሰድ እርምጃ ባለመኖሩ ችግሩ መፍትሄ ሳያገኝ የሚቀጥልበት ሁኔታ በመኖሩ ግጭቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የህዝቡ የልብ ትርታና የመንግስት የማስፈፀም አቅም ተጣጥሞ ሊሄድ አልቻለም፡፡ ስለዚህ ህዝቡ ተስፋ የመቁረጥና ይፈታል ወይ የሚል የጨለምተኝነት ስሜት መፈጠርና የደህንነታ ሥጋት መኖር ይታያል፡፡

## 1.6 የሃገሪቱ ገፅታ እየተበላሸ ነው

ሃገራችን ባስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ያለውን ሰላምና መረጋጋት ለሁሉም ጎረቤቶቻችን ሆነ ሌሎች በሞዴልነት የሚጠቀስና ገፅታችንን የቀየረ፣ ፍፁም የተረጋጋች ሃገር እንድትሆን አድርጓት ቆይቷል፡፡

የፌዴራል የፀጥታ ኃይሎቻችንም በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ተወዳዳሪና ተፈላጊ ኃይል እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በዚህ ምክንያትም ከፍተኛ የሆነ የቱሪስት ፍሰትና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንዲኖር አድርጎት ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ወቅት በተፈጠረው ያለመረጋጋትና ለረጅም ጊዜ ሳይፈታ መቆየቱ የተለያዩ አመለካከቶች እየተፈጠሩ ናቸው፡፡ የሃገራችን ወዳጅ ሃገሮችና ጎረቤቶቻችን ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ለኛም አደጋ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መረጋጋት ከራሳቸው ህልውና ጋርም በማያያዝ ሰላሙን ወደነበረበት እንዲመለስ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው፡፡

ጠላቶቻችን ደግሞ ሁኔታው እንዲባባስና ሃገሪቱ እንድትበታተን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሁሉንም አቅማቸው አሟጠው ሌት ተቀን በታቀደ መንገድ እየመሩበትም ይገኛሉ፡፡

## 1.7 ግጭቶቹ የመቆም አዝማሚያ አይታይባቸውም

ግጭቶቹ ቶሎ የመቆም አዝማሚያ አይታይባቸውም፤ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ፡-

1. በየደረጃው ያለ አመራር ችግሩ የኔ ነው ብሎ በባለቤትነት ከመፍታት ይልቅ በዚህ ችግርና ኋላቀርነት መኖር ስለጀመረና እንደ ዋሻ (መደበቂያ) ስለሚጠቀምበት፣
2. ህዝብ የሚል አጀንዳ ቀርቶ በምትኩ ኪራይ ሰብሳቢነት እያደገ ስለመጣ፣
3. እስካሁን በተፈፀሙ ጥፋቶች ላይ ወንጀለኞችና እጃቸውን ያስገቡ አመራር አካላት በህግ ስላልተጠየቁና መሠረታዊ መፍትሄ ስላልተደረገለት በቀላሉ ይቆማል ተብሎ አይታሰብም፡፡

**አሁንም**

- ከፍተኛ የሆነ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት እየተካሄደ ነው፣ አልቆመም፣
- ከፍተኛ የመሳሪያና ተተኳሽ ግዥና ፍሊጋ አለ፣
- ከፍተኛ ገንዘብ ለጦርነቱ እየተሰባሰበ ነው፣

Addis Standard

- ብዙ ኃይልም እያሰባሰቡ ናቸው፣
- በዚህ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ህገ-ወጥ የመሳሪያ ዝውውርም እየተስፋፋ ነው፣
- ያለመተማመንና መካካድ ጭምር ስላለ ከመሰረቱ ታይቶ ካልተፈታ የመቆም ሁኔታ አይታይበትም፡፡
- ሂዶ ሂዶ ደግሞ ወደ ነውጥና ብጥብጥ እንደሚሸጋገር መገመት ይቻላል፡፡

## 1.8 ህዝቡ ሥጋት ውስጥ ወድቋል

ህዝቡ አሁንም የመፍትሄው ባለቤት ሆኖ ሰላሙን ወደነበረበት እንዲመለስ ለፌዴራል መንግስት ይጮሃል ፡፡

ውስጥ ለውስጥም በሽማግሌዎች አማካኝነት እየተገናኘ ግጭቱ እንዲቆም ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል፡፡

Addis Standard

ሰዎች እንዳይገደሉ ይደብቃል፣ ምግብ፣ ውሃ ይሰጣል፡፡

የውጊያ ቅስቀሳና ጩኸት ጆሮ ዳባ በማለት ወደ ልማቱ ይሰማራል፡፡

ይሁን እንጂ በከፍተኛ አሉቧልታና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በመደናገር፣ መንግስት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ባለመኖራቸውና የህግ የበላይነት ሳይከበር ስለቀረ ለመሆኑ ችግሩ ይፈታል ወይ? ሰላሙ ተመልሶ ይመጣል ወይ? ከሚል ተስፋ መቁረጥና ስጋት ውስጥ የመውደቅ ሁኔታ ይታያል፡፡

## 1.9 የችግሩ ባለቤት አሁንም አመራሩ ነው

አመራሩ በኋላ ቀርነትና በችግር ውስጥ ተደብቆ ለመኖር ከመፈለግ አኳያ ችግሮቹ እንዳይፈቱ በተለያየ መንገድ እንቅፋት እየፈጠረ መንግስት በዚህ አዙሪት እንዲኖር እያደረገ መሆኑ፣

ህዝቡንና ወጣቱን ለልማትና ለሰላም ከማዝመት ይልቅ ወደ ጦርነት ማዝመትና ከዋና አጀንዳው እንዲወጣ ማድረግ፣

ያልጠራ አመለካከት መያዝ፣ የጎራ መደበላለቅ መኖርና የኪራይ ሰብሳቢነትና ጥገኛ አመለካከት መስፋፋት፣

የተልዕኮ አልበኝነት አስተሳሰብ መኖርና ለመበስበስ አደጋ መጋለጡ ናቸው፡፡

## 1.10 የፀጥታ ኃይሎችን ዝግጁነት በከፍተኛ ሁኔታ እየጎዳ ነው

የፀጥታ ሃይላችን ሁከትና ብጥብጥ ለማረጋጋት ለበርካታ ጊዜያት በየበረሃው ሲንከራተት፣ ሲራብ፣ ሲታረዝ፣ ሲቆስልና ህይወት ሲከፍል ቆይቷል፤ አሁንም ከዚህ ሁኔታ አልወጣም፡፡

ነውጥና ብጥብጥ ለማስቆም፣ የክልሎች ወሰን ለመጠበቅ ሲባል ከዋናው ተልዕኮና ግዳጅ እየወጣ በረባና ባልረባ ተጠምዶ ቆይቷል፡፡

የክልሎች ፀጥታ ሃይልም በተለያየ ምክንያት በየአካባቢያቸው የተፈጠረውን የፀጥታ ችግር መፍታት አለባቸው፡፡ ህብረተሰቡም የፀጥታ ዋስትና አጥተዋል፡፡

Addis Standard

በዚህ ምክንያትም ችግሩ ለምን አይፈታም፣ እስከ መቼ እንደዚህ ብለን እንኖራለን፣ ለመሆኑ ይፈታል ወይ? ከሚል የመሰላቸት፣ ተስፋ የመቁረጥና የመጨለም አዝማሚያ እየታየበት ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ እያለ ሌሎች ተጨማሪ አሉቧልታዎች ሲጨመሩበት ደግሞ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

ስለዚህ የክልሎች የፀጥታ ሃይሎች በአቅም በአስተሳሰብ እንዲጠናከሩ ማብቃትና ማጠናከር ቀጥሎ የአካባቢያቸውን ፀጥታ በራሳቸው እንዲያስከብሩ ማድረግ፡፡ መደበኛ ሠራዊትም ወደ መደበኛ ስራው እንዲገባ ማድረግ ይሆናል፡፡

## III. የሁኔታ ድምዳሜ

**1. የፌዴራል ስርአቱ አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ክስተቶች እየታዩ ናቸው፡፡**

- ስርአት አልበኛነትና እምቢተኛነት እየተስፋፋ ነው፡፡
- የህግ የበላይነት እየተተገበረ አይደለም፡፡

**2. ህዝባችን ስጋት ላይ ወድቋል**

- ለመሆኑ ችግሩ ይፈታል ወይ ብሎ ተስፋ የመቁረጥና የሰላም ዋስትና አጥተዋል፡፡ በስጋቶች እየኖረ ይገኛል፡፡

**3. ፀረ-ሰላም ሃይሎች ስርአቱን ለማፍረስ እየተረባረቡ ናቸው**

- የተፈጠረውን ያለመረጋጋት እንደምቹ ሁኔታ በማየት የውስጥም የውጭም ተቀናጅተው በስትራቴጂም ሆነ በስልት ተደራጅተው ስርአቱን ለማፍረስ ሌት ተቀን እየተረባረቡ ናቸው፡፡

**4. የችግሩ ባለቤት አሁንም አመራሩ ነው**

- አመራሩ በኋላ ቀርነትና በችግር ውስጥ ተደብቆ ለመኖር ከመፈለግ የችግሮቹ ፈጣሪና መሪ ችግሮቹ እንዳይፈቱም በተለያየ መንገድ እንቅፋት እየፈጠረ መንግስት በዚህ **አዙሪት** እንዲኖር እያደረገ መሆኑ፣
- ህዝቡንና ወጣቱን ለልማትና ለሰላም ከማዝመት ይልቅ ወደ ጦርነት ማዝመትና ከዋና አጀንዳው እንዲወጣ ማድረግ፣
- ያልጠራ አመለካከት መያዝ፣ የጎራ መደበላለቅ መኖርና የኪራይ ሰብሳቢነትንና ጥገኛ አመለካከት መስፋፋት፣
- የተልእኮ አልበኝነት አስተሳሰብ መኖርና የመበስበስ አደጋ መጋለጥ ናቸው፡፡

## IV. ከድምዳሜ የሚነሳ ዕቅድ

**ከዚህ ድምዳሜ በመነሳት በፀጥታ ሃይላችን መሰራት ያለባቸው ስራዎች**

- ከድምዳሜ እንደተረዳነው ችግሩ ፖለቲካዊ መሆኑ መፍትሄውም ፖለቲካዊ መፍትሄ የሚሻ መሆኑ ተቀምጧል፡፡
- ይሁን እንጂ ችግሩ እንዳይሰፋና እንዳይቀጥል ለመግታትና ለሚሰሩ ፖለቲካዊ ስራዎች ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር አንፃር የሚከተሉትን ስራዎችን ሁሉም የፀጥታ ሃይሎች በጋራ እቅዱን በተደራጀ መስራት ያለባቸውን ስራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## V. ዓላማ

- ህግና ስርዓት እንዲሰፍን በማድረግ መንግስትና ህዝቦች ለሚሰሩት የልማትና መልካም ማስተዳደር እንቅስቃሴዎች የተረጋጋና አስተማማኝ ሰላም መፍጠር፡፡

Addis Standard

VI. **ግቦች**

**ግብ (1)**

- የህዝቦችን ነፃ ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ መብታቸው እንዳይገደብ ማድረግ (መስራት)፡፡

**ግብ (2)**

- ዋና ዋና መስመሮች ያለምንም የፀጥታ እንቅፋት እንዲሰሩ ማድረግ፡፡

Addis Standard

**ግብ (3)**

- ጥፋተኞች፣ ወንጀለኞችና አሸባሪዎች መለየትና መቆጣጠር ልህግ ማቅረብ፡፡

**ግብ (4)**

- ህጋዊ ያልሆነ ሰልፍ መቆጣጠር፡፡

**ግብ (5)**

- የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በሰላም ወደሚፈልጉት እንዲንቀሳቀሱ የፀጥታ ስጋት እንዳይኖራቸው ማድረግና ሌሎችን አስፈላጊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ከሚመለከታቸው አካሎች በጋራ መስራት፡፡

**ግብ (6)**

- የታጠቀ ፀረ-ሰላም ሃይሎችን መቆጣጠር፡፡

**ግብ (7)**

- ህገ-ወጥ የመሳሪያ፣ የሰው ዝውውርና ኮንትሮባንድን መቆጣጠር፡፡

**ግብ (8)**

- ሁሉም የፀጥታ አካሎች መዋቅር ማጠናከር መደገፍ፡፡

## VII. <u>ግቦችን ለማሳካት የሚሰሩ ስራዎች</u>

### <u>ግብ (1)</u>

- ችግር ባለባቸው አካባቢዎች በቂ የፀጥታ ሃይል በመመደብ ሌሎች ለግጭት ችግር ይፈጥራሉ የተባሉ የክልሎች ፀጥታ ሃይል ከአካባቢው እንዲነሳ ማድረግ፣ ግልፅ የሆነ የታጠቀው ሃይል የሚንቀሳቀስበትን ቦታ መለየትና መወሰን መተግበር፡፡
- ብዙ አመታት በጋራ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች አሁን ሰላማቸው እንደተለመደው እንዲቀጥል ተሰሚነት ያላቸውን ሽማግሌዎች በመነጋገርና በማሰባሰብ እርቅ እንዲፈፅሙና ጥፋተኞችን ለፀጥታ ሃይል አሳልፈው እንዲሰጡ መስራት፡፡
- ሌሎች የህዝብን ነፃ እንቅስቃሴ የሚከለክል ወይም ለግጭት የሚያነሳሱ ቡድን ይሁን ግለሰቦች መለየት መቆጣጠርና ለህግ ማቅረብ፡፡

Addis Standard

### <u>ግብ (2) ዋና ዋና መስመሮች ያለምንም የፀጥታ ችግር 24 ሰዓት እንዲሰሩ ማድረግ</u>

- መስመሮችን መለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ፓትሮል ማድረግ፣ ለአካባቢው ህብረተሰብና ፀጥታ ሃይል ቦታዎችን ከፋፍሎ መስጠትና መምራት መቆጣጠር፡፡
- ለመስመሮች አደጋ የሆነ የተጠኑና የሚታወቁ ካለም አስቀድሞ መፍታት፡፡
- ወደ ጎረቤት ሀገሮች መውጫና መግቢያ የሆኑትን ቁልፍ ቦታዎች በቋሚና በተንቀሳቃሽ ጥበቃ ማድረግ፡፡

### <u>ግብ (3) ጥፋተኛ፣ ወንጀለኞችና አሸባሪዎች መለየት መቆጣጠር</u>

- በሰው በንብረት ውድመትና ጭፍጨፋ የፈፀሙ
- በተለያየ መንገድ ህብረተሰቡን ለጦርነት የቀሰቀሱ
- በህዝቦች መተማመን አንድነት እንዳይኖር ፀረ-ህዝብ ቅስቀሳዎችን ያካሄዱ
- ለፀረ-ህዝብ ተግባር የሚውል የንብረትና የገንዘብ መዋጮ ያደረገ

### <u>ግብ (4) ህጋዊ ያልሆነ ሰልፍ መቆጣጠር</u>

- በየትኛውም መንገድ ሰልፍ በማድረግ ለሰው ህይወት መጥፋት፣ ንብረት መውደም ምክንያት የሆኑ ሰልፎች እንዳይደረጉ መከላከል ከተደረጉም በሰልፉ አነሳሺዎች አስተባባሪዎች ህጋዊ እርምጃ መውሰድ (በቁጥጥር ስር ማድረግና ለህግ ማቅረብ)

ህዝባችን ለዘመናት የቆየውን የመቻቻል፣ የመከባበርና የአብሮነት እሴቱ ጠንካራና ቀጣይነት ያለው መሆኑ፣

የአካባቢውን ሠላም፣ ፀጥታና ደህንነት ለማስጠበቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባባሪ በመሆን ሊደርሱ የሚችሉትን የሽብር ጥቃቶች በማውገዝም ሆነ በመከላከል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑ፣

ሰላም እንዲሰፍን የትግሉ ባለቤት መሆኑ፣

ፌደራሊዝምን እንደ ዋስትና የሚያይና የዚህ ባለቤት መሆኑ፣

በርካታ ወጣት ከስራ እጥነት ወደ ልማት እየገባ ያለ መሆኑና ነውጥንና ግጭትን የማይፈልግ መሆኑ፣

## 8.2. የውጭ ፀረ-ሰላም ሃይሎች ተፅዕኖና ትኩረት አናሳ መሆን

ዋናው ችግር ውስጣዊ እንጂ ውጫዊ ያለመሆኑና ከባድ ተፅዕኖ እንደማይፈጥርና ከቁጥጥር ውጭ እንደማይሆን፣

ውስጣዊ ገፅታችን ከተስተካከለ ተያይዞ የሚስተካከልና ለመታገልም ምቹ ሁኔታ መኖሩ፣

## 8.3. የፀጥታ አካላት የመፈፀም አቅማችንና ውስጣዊ ሁኔታችን እስተማማኝ መሆን

Addis Standard

የፀጥታ ሃይሉ ከህዝቡ አብራክ የወጣ ምንጊዜም ለሃገሩና ለህዝቡ መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀና ጠንካራ ህዝባዊ ወገንተኝነት የተላበሰ መሆኑ፣

ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን ለመጠበቅ በላቀ ጀግንነት የመፈፀም አቅሙና ችሎታው እየዳበረ የመጣ መሆኑ፣

ወትሮ ዝግጁነቱንና ዴሞክራሲያዊ ግንኙነት በማጠናከር ከጊዜ ወደ ጊዜ የግዳጅ አፈፃፀሙን በመገምገም ለላቀ ግዳጅ ዝግጁ የሆነ ሃይል መገንባቱና በታጠቃቸው ቴክኖሎጂዎች የመጠቀም አቅሙን እያሳደገ የመጣ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

### ፱.፬. መንግሥት ችግሮችን የመፍታት አቅምና ተሞክሮ ያለው መሆኑ

ዘላቂ የሰላምና የልማት ግቦችን በማሳካት፣ በማኅበረሰቡና የመንግሥት አካላ በማድረግ፣

በየክልሉ ደግሞ በዘር የተገለ ባለቤት በማድረግ ወደ ቀዬው ለማ (ድብቅ) እንዲዘዋወሩ በመምራት፣

ችግሩ ፖለቲካዊ ስለሆነ መፍትሔውም ፖለቲካዊ ነው በሚል በማመንና በመደገፍ በአጭር ጊዜ ችግሩን ለመፍታት ምቹ ሁኔታዎች መፍጠሩ ግዴታ ይሆናል።

## ፲. የአፈጻጸም አቅጣጫ

Addis Standard

1. [illegible] በመሰረቱ መፈታት [illegible]።
2. የህዝብ አስተያየት በቅንጅትና በጋራ መስራት
   - ሀ. ስራ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም
   - ለ. በቀጣናዎቹ የጋራ እቅድ መያዝ
   - ሐ. የተግባርና የአስተዳደር አንድነት በመፍጠር ውጤታማ ስራ መስራት
3. ችግሮቹ በላቀ ደረጃ ለመፍታት ያሉትን ምቹ ሁኔታዎች አሟልቶን መጠቀም።
4. ግልፅ የሆነ አሰራርና ደንብ ወደ ተግባር መግባት (የተደራጀ) አስተዳደር ደንብን ወደ ስራ አለመግባት።
5. የተፈጠሩ ችግሮች ዘላቂ ጊዜ እንዳይመለሱ የሚያደርግ የሰው ኃይል አፈጻጸም መከተል።

## XI. ዝርዝር አፈፃፀም

1. በየቀጠናው ያሉ የፌደራልና የክልል የፀጥታ አካሎች የአካባቢውን ሁኔታና የፌደራል ዕቅድ መነሻ ያደረገ የጋራ ዕቅድ ያወጣሉ፡፡
2. በተዘጋጀው ዕቅድና አፈፃፀም በጋራ ግልፅ ኦረንቴሽን በመስጠት በሁኔታና በትግበራ ላይ አንድ አይነት አረዳድ መፍጠር፡፡
3. በየአካባቢው የሚደራጀው ኮማንድ ፖስት (ጥምር ኮሚቴ) በጋራ ስራዎችን ይፈፅማል፣ ይመራል፣ ለሚመለከተው አካል በየጊዜው ሪፖርት ያደርጋል፡፡
4. የኮማንድ አደረጃጀት አመራርና ቁጥጥሩ እንዴት ይሆናል የሚል በአባሪ ይገለፃል፡፡

Addis Standard

በፌዴራል የብ/ደህንነት ምክር ቤት እና በክልል የፀጥታ ም/ቤቶች መካከል

የሥራ ግንኙነት [illegible]

Addis Standard

ጥቅምት 30/2010 ዓ/ም

5. <u>የጊዜ ሠሌዳ፤</u>

- በሀገር ደረጃ የጋራ መድረክ የመወያየት በ1/03/2010

  **<u>ፈፃሚ፦</u>** ጠቅላይ ሚ/ር፤

  በክልል ደረጃ የየክልሉን እቅድ ተወያይቶ በጋራ የማፅደቅ ሥራ ከ10-15/03/2010

  **<u>ፈፃሚ፤</u>** - የየክልሉ ርዕሰ መስተዳድር /ፕሬዝዳንት፣

- ተመሳሳይ አደረጃጀትና እቅዶች እስከታችኛው እርከን የመፍጠርና የየራሳቸውን እቅድ አዘጋጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ ማጠናቀቅ፤ **16-20/03/2010**

  **<u>ፈፃሚ፤</u>** - በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች፤

- የፀደቀ የክልሉን የፀጥታ እቅድ ለማዕከል መላክ፣

  **16/03/2010**

Addis Standard

- ወርሃዊ ሪፖርት ወር በገባ በ5 ይላካል ለማዕከል፤
- ወርሃዊ የጋራ ስብሰባ በፌደራል ደረጃ በየወሩ ሁለተኛ ሳምንት ባሉት ቀናት ይሆናል፡፡